የዲሲ የስቴት ትምህርት የበላይ ሹም ጽ/ቤት

# ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ መርዳት

## ለአዲሱ የPARCC ማጣሪያ የተዘጋጀ መመርያ

የዲሲ ህዝባዊ እና ህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ለ2014-15 የትምህርት ዘመን ወደ የኮሌጅ እና ሞያ ዝግጁነት ማጣሪያ ፈተና ሽርክና [Assessments of Readiness for College and Careers (PARCC)] እየቀየሩ ናቸው፡፡ ይህ አዲስ ፈተና የዲሲው አጠቃላይ ማጣሪያ ሲስተም [DC Comprehensive Assessment System (DC CAS)] የሂሳብ፣ ንባብ፣ እና ጽሁፍ ፈተናዎችን ይተካል፡፡ አዲሱ ፈተና ከባድ ይሆናል፤ ጠቃሚ የሆኑ የተማሪ ዕድገት ምዘናዎች ያቀርባል፤ እንዲሁም የዲሲ የስቴት ትምህርት የበላይ ሹም ጽ/ቤት (OSSE) እያንዳንዱ ተማሪ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለኮሌጅ ወይም ሞያ ዝግጁ በሆነ መልኩ እንዲያጠናቅቅ ለማረጋገጥ ከሚሰራቸው ሥራዎች አንዱ መንገድ ነው፡፡

## PARCC አስመልክተው በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

### 1 PARCC ምንድን ነው?

PARCC “ምላሽ-ሰጭ” የሆነ፣ በኮምፒዩተር ድጋፍ የሚሰጥ ፈተና ሆኖ የስቴት የተለመዱ ዋና ስታንዳርድ/መመዘኛዎችን የተከተለ ነው፡፡ ይህ ፈተና ከ3ኛ እስከ 8ኛ ክፍል እና ቢያንስ አንዴ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ውስጥ የተማሪን የንባብ፣ ጽሁፍ፣ እና ሂሳብ ትምህርት ችሎታን የሚለካ ይሆናል፡፡

### 2 PARCC ከDC CAS በምን ይለያል?

- PARCC የስቴት የተለመዱ ዋና ስታንዳርድ/መመዘኛዎችን የተከተለ ነው (DC CAS ይህንን የተከተለ አልነበረም)፡፡
- ተማሪዎች የPARCC ፈተና ለመውሰድ ቴክኖሎጂ (ለምሳሌ፣ ዴስክቶፕ ኮምፒተሮች፣ ላፕቶፖች፣ እንዲሁም/ወይም ታብለቶች) ይጠቀማሉ፡፡
- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚቀርቡላቸው መመሪያዎች መሰረት ጽሁፍ ያነባሉ እንዲሁም ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡
- ተማሪዎች ትክክለኛውን መስል ከመምረጥ ባሻገር ቅማሬያዊ/ሂሳብ-ነክ አስተሳሰብ እንዲያስረዱ ይጠየቃሉ፡፡
- ተማሪዎች ውስብስብ የሆኑ ምንባቦችን እንዲያነቡ እና መከራከርያ ነጥቦች ሊሆኑ የሚችሉ እውነታዎችን እንዲለዩ ይጠየቃሉ፡፡

### 3 የPARCC ጠቀሜታዎች ምንድን ናቸው?

- ቤተሰቦች ስለ ተማሪው ዕድገት ግልጽ መረጃ ያገኛሉ፡፡
- አስተማሪዎች የማስተማር ሂደትን እና መመሪያን ለመቀየስ ወቅታዊ ዳታ እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል፡፡

### 4 የPARCC ፈተና እንዴት የሰጣል?

PARCC በሁለት ይከፈላል፡-

1. በውጤት የተመረኮዘ ግምገማ [Performance Based Assessment (PBA)] - ጽሁፍ፣ የጥናት ክህሎቶች፣ እንዲሁም ብዙ ደረጃ የሚጠይቁ የሂሳብ ስሌት ጥያቄዎችን ይመዝናል፡፡ የፈተና ቀን፡- የስፕሪንግ መጀመርያ
2. የዓመት መጨረሻ ግምገማ [End of Year (EOY) Assessment] - የጽሁፍ መለማመጃ ንባብ እና የሂሳብ ሥነ- ሀሳቦችን እና ክህሎቶችን በባለ ብዙ ምርጫ እና አጭር መልስ የሚሰጡባቸው ጥያቄዎች መልክ ይለካል፡፡ የፈተና ቀን፡- የስፕሪንግ መጨረሻ ገደማ፡-

### 5 PARCC የሚያቀርባቸው ለመጠቀም የሚቻሉ አገልግሎቶች ምንድን ናቸው?

የPARCC ፈተና ለተማሪዎች የተቻላቸውን ያህል እንዲሰሩ የሚረዱ መሳሪያዎች ያቀርባል እንዲሁም በተለያዩ አቅርቦቶችን በኩል የIEP (በግል የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም) ወይም የ504 ዕቅድ ያላቸው እና የኢንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች (ELL) እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡

### 6 የPARCC ፈተና በሚሰጥበት ወቅት፣ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- በስክሪን ላይ ያለውን ጽሁፍ ለመቀባት የሃይላይተር መሳርያ መጠቀም፤
- የፈተና መመሪያዎች እንደአስፈላጊነቱ በከፍተኛ ድምጽ እና በተደጋጋሚ እንዲነበቡ ማድረግ፤
- የጽሁፎች እና ምስሎች ቅርጽ ማሳደግ፤
- ስፔልቸከር መጠቀም፤
- በአዲስ ገጽ የሚከፈት መዝገበ-ቃላት መጠቀም፤
- በስክሪን ላይ በሚገኝ የማስታወሻ መያዣ (ኖትፓድ) ላይ ማስታወሻ መያዝ፤
- ተመልሰው ማየት የሚፈልጉትን የባንዲራ ምልክት መስጠት፤ እንዲሁም
- ለባለ ብዙ ምርጫ ጥያቄዎች መልሶችን በመሰረዝ መመለስ፡፡

### 7 ስለ የስቴት የተለመዱ ዋና ስታንዳርድ/መመዘኛዎችን የሚከተሉትን በማድረግ የበለጠ ይረዱ፡-

- ልጅዎ ምን እየተማረ እንደሆነ እና እነዚያን ጥረቶች በቤት ውስጥ እንዴት መርዳት ይቻላል የሚለውን በሚመለከት የልጅዎ አስተማሪዎችን ማነጋገር፡፡
- የልጅዎ አስተማሪዎች ለአዲሶቹ ግምገማዎች እንዴት እየተዘጋጁ መሆናቸውን እና ልጅዎ ዝግጁ እንዲሆን በምን መልክ እየረዱት እንደሆኑ መጠየቅ፡፡
- ልጅዎ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙባቸው

### የዲሲ አዲስ ግምገማ ቀነገደብ፡-

**2014-2015**

- PARCC ምንባብን፣ ሂሳብን እና ድርሰትን በተመለከተ DC CASን ይተካል፡፡
- ከመጪው ትውልድ የሳይንስ ስታንዳርድ ጋር የተስተካከለ አዲስ የሳይንስ ፈተና የDC CAS የሳይንስ ፈተናን ይተካል፡፡
- አዲስ የጤና ፈተና የDC CAS የጤና ፈተናን ይተካል፡፡
- National Center State Collaborative (NCSC) ከባድ የመረዳት እክል ላላቸው ተማሪዎች የተዘጋጀውን የDC CAS-አማራጭን ይተካል፡፡

**2015-2016**

- ELsን በቴክኖሎጂ አማካኝነት የሚደግፉ የግምገማ አገልግሎቶች [Assessment Services Supporting ELs through Technology Systems (ASSETS)] ከስቴት ወደ ስቴት የጽሁፍ መለማመጃ እና ንግግር መገምገምን [Assessing Comprehension and Communication in English State to State (ACCESS)] በመተካት የዲሲ የኢንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት መገምገሚያ ይሆናል፡፡



810 1st Street NE, 9th Floor, Washington, DC 20002 USA • 202.727.6436 • osse.dc.gov • parcconline.org